# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com


## የሁሉም የህሊና እስረኞች መፈታትና የዜጎች ሰብዓዊ መብት መከበር፣ ሙሉ ምላሽ የሚሻ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄ ነው።

ሐምሌ 2፣ 2007 ( ጁላይ 9፣ 2015)

ከዓመት በላይ ያለአግባብ አስሯቸው ካቆየ በሁዋላ የወያኔ/ ኢህአዴግ መንግስት ጦማሪያን ኤዶም ካሳዬን ዘላላም ክብረትን፣ ማህሌት ፋንታሁንን እንዲሁም ጋዜጠኛ ተስፋለም ወልደየስና አስማማው ሀይለጊዮርጊስን ትላንት ሀምሌ 1 ፣ 2007 ( ጁላይ 8፣ 2015) በዛሬው ዕለት ደግሞ ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙን ካመታት እስር በሁዋላ ድንገት እንደፈታቸው ታውቋል።

ግለሰቦቹ ቀድሞም የታሰሩት የጋዜጠኛ ሙያቸውን ሲወጡና ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብታቸውን ተግባራዊ በማድረጋቸው እንጂ ሌላ ወንጀል ፈጽመው አልነበረም። በመሆኑም እንኳንስ ለረጅመ ጊዜ ለአንድ ሰአትም ቢሆን መታሰር አይገባቸውም ነበር። የስርአቱ የጸጥታ ሀይሎችና ካድሬዎች በዚሁ የጥፋት ጎዳና በመቀጠል ባለፉት ጥቂት ወራት ብቻ በሰላዋሚ መንገድ ለመብታቸው የቆሙ እጅግ ብዙ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች (በተለይም የመድረክ የሰማያዊ ፓርቲና የመኢአድን) አባላትና ደጋፊዎች አስረዋል፤ ደብድበዋል፤ ገድለዋል። ይህን ቀጣይ የመብት ረገጣ ሸንጎው በጥብቅ ያወግዛል።

ከላይ የተጠቀሱት ስድስት ግለሰቦች ከእስር መፈታት የሚደገፍ ሲሆን የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት በተመሳሳይ ሁኔታ በየእስር ቤቱ በሰበብ ባስባቡ አፍኖ እያሰቃያቸው የሚገኙትን እነ እስክንድር ነጋ፣ ተመስገን ደሳለኝ ፣ ውብሸት ታየና ሌሎችንም ጋዜጠኞች እንዲሁም አንዱአለም አራጌ፣ ሀብታሙ አያሌው፤ አቡበከር አህመድ፤ አብርሀም ደስታን፤ የሸዋስ አሰፋ፣ ዳንኤል ሸበሽ፤ አልባና ለሊሳና በሸዎች የሚቆጠሩ ሌሎችንም የፖሊተካ እስረኞች ባስቸኳይ እንዲፈቱ፤ ከየቦታው ተወስደው ከዘመድ አዝማድና ከህዝብ እንዲሰወሩ የተደረጉ ዜጎች የት እንደደረሱና በምን ሁኔታ እንደሚገኙ እንዲያሳውቅ ሸንጎው አጥብቆ ይጠይቃለ። ባጠቃላይም ኢትዮጵያ ዛሬ ከገባችበት ችግር እንድትወጣ ይቻላት ዘንድም ገዥው ቡድን በዜጎች ላይ የሚያካሄደውን የመብት ረገጣ ባስቸኳይ እንዲያቆምና ያሉትን ችግሮች ለመፍታትም ሆነ የወደፊቱን ዕክል ለመቋቋም ብሄራዊ መግባባትና እርቅን መሠረት በማድረግ እንዲነሳ አሁንም እናሳስባለን።

ድል ለኢትየጵያ ህዝብ


Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : **shengo.derbiaber@gmail.com**